**በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሱፒሪየር ፍርድ ቤት**
**የባለ ብዙ-በር አለመግባባት መፍቻ ክፍል (መልቲ-ዶር ዲስፒዩት ሪሶሊሽን ዲቪዥን)**

የሽምግልና ሂደቶች- ለጠበቆች

ሽምግልና እንዲሳተፉ ላዘዛቸው ሁሉንም ጉዳዮች ፍርድ ቤቱ የሚከተሉት ሂደቶች አዘጋጅቷል። የጉዳዮቹ አካላትና ጠበቆቻቸው እነዚህን ሂደቶች ባይከተሉ እገዳዎች ሊጣሉባቸው እንደሚችሉ ከወዲሁ እንዲገነዘቡ ማስጠንቀቅ እንፈልጋለን።

**<u>*ለሽምግልና ለመዘጋጀት መወሰድ ያለባቸው ነገሮች*</u>**

**1. ሁሉም አካላት ለሽምግልና መቅረብ ይኖርባቸዋል፡** ሁሉም ጠበቆችና ደምበኞቻቸው፣ አስቀድሞ በዳኛው እንዳይሳተፉ የተፈቀደላቸው ካልሆነ በስተቀር፣ ለሽምግልና በባለ ብዙ-በር አለመግባባት መፍቻ ክፍል በጉዳዮ በተሰጠው የመርሀግብር ትእዛዝ (ስኬጁሊንግ ኦርደር) መሰረት መቅረብ ይኖርባቸዋል። አካላቱ ለሽምግልና ካልቀረቡ ሽምግልናው መካሄድ አይችልም፣ በተጨማሪ "አለ መምጣትዎ" ለዳኛው ቢሮ (ቻምበርስ) ይነገረዋል።

ከፍተኛ መቶኛ ለሽምግልና ከተመሩ የፍትሐብሔር ጉዳዮች፣ ውድ እና ጊዜ አባካኝ ክርክር ሳያስፈልጋቸው፣ በአስደማሚ ሁኔታ በስምምነት እንደሚፈቱ የአገር አቀፍ ተመኮሮ በሰፊው ያሳያል። *ሁሉም* የጉዳዩ አካላት ገለልተኛ አካል ባለበት ፊት-ለፊት ለውይይት ሲቀመጡ በስምምነት የመፍታቱ እድል ይጨምራል። የኢንሹራንስ ድርጅት ያለበት ጉዳይ ቢሆንም እንደዚሁ ነው።

- ኮርፖሬሽኖች ፣ ሽርክናዎች እና ሌሎች የንግድ አካላት፣ አስቀድሞ በዳኛው እንዳያመጡ ፈቃድ የተሰጣቸው ካልሆነ በስተቀር፣ ስምምነት የማድረግ ስልጣን ያለው ኦፊሰር፣ ሽርካ ወይም ሌላ ግለሰብ ይዘው መምጣት ይኖርባቸዋል። ዳብሊው.ኤም.ኤ.ቲ.ኤ.፣ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ እና ሌሎች አካላት፣ በዳኛው እንዳያመጡ ፈቃድ የተሰጣቸው ካልሆነ በስተቀር፣ ጉዳዩን ለመፍታት ስልጣኑ ሊያስፈልግ የሚችል ተወካይ መላክ ይኖርባቸዋል።

- ዳኛው የፈቀደ ከሆነ፣ ጉዳዩ በስምምነት ለመፍታት ሙሉ ስልጣን ያለው የኢንሹራንስ ተወካይ ኢንሹራንስ ያለውን አካል ወክሎ በኮንፈረንሱ መሳተፍ ይችላል።

- ዳኛው እንዳይሳተፍ የፈቀደ ካልሆነ በስተቀር፣ ጉዳዩ በስምምነት ለመፍታት ስልጣኑ ሊያስፈልግ የሚችል የኢንሹራንስ ተወካይ በሽምግልና መሳተፍ ይኖርበታል። Super. Ct. Civ. R. 16 (j) *ይመልከቱ።*

- በአካል ላለመሳተፍ ከዳኛ ፈቃድ የተሰጠው ከሜትሮፖሊታን አከባቢው ውጪ የሚኖር አካል ወይም የኢንሹራንስ ተወካይ በመላው የሽምግልና ክፍለ ጊዜ በረጅም-ርቀት ስልክ ሊገኝ ይገባል። በአካል

ያልመጣው አካል ጠበቃ ወይም የኢንሹራንስ ተወካይ ባለ ብዙ-በር ክፍልን ስለ ተደረገው ዝግጅት ማሳወቅ፣ በስልክ የሚገኘውን አካልም ስም ማቅረብ ይኖርበታል። Super. Ct. Civ. R. 16 (j) *ይመልከቱ።*

**2. ጠበቆች ኤም.አር.ሲ. እና ሲ.ኤስ.ኤስ. ማስገባት ይኖርባቸዋል፡** ሽምግልና ከሚደረግበት 14 ቀን አስቀድመው ጠበቆች የተያያዘውን "የሽምግልና ዝግጁነት የምስክር ወረቀት" እና "ምስጢራዊ የስምምነት መግለጫ" ለባለ ብዙ-በር አለመግባባት መፍቻ ክፍል- Multi-Door Dispute Resolution Division, 410 E Street, N.W., Suite 2900, Washington, D.C. 20001፣ ወይም በኢሜይል ለ፡ CivilMRC-CSS@dcsc.gov ማስገባት ይኖርባቸዋል። ለበለጠ ዝርዝር የተያያዙት ፋይል ማድረጊያ መመሪያዎች ይመልከቱ። **የሽምግልና ዝግጁነት የምስክር ወረቀት እና ምስጢራዊ የስምምነት መግለጫ ቅጂዎች ወደ ክለርክ (ጸሐፊ)፣ ለተመደበው ዳኛ፣ ወይም ሌሎች ጠበቆች/አካላት አይላኩ።**

**3. ኤም.አር.ሲ. እና ሲ.ኤስ.ኤስ. ካላስገቡስ፡** መረከብ ያለባቸው ቅጾች ባያስረክቡ ሽምግልናው ተሰርዞ እገዳ ለምን መጣል እንደሌለበት እንዲያብራሩ ጉዳዩ በሚያየው ዳኛ ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚታይበት ቀጠሮ (ስታተስ ሂሪንግ) ሊያዝ ይችላል። የሚወከሉት አካላት በመግለጫው በግልጽና በዝርዝር እስከቀረቡ ድረስ፣ ጠበቆች ለሁሉም የሚወክሏቸው አካላት አንድ የሽምግልና ዝግጁነት የምስክር ወረቀት እና ምስጢራዊ የስምምነት መግለጫ ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

**4. ለሽምግልና ቅረብ የተባልኩት በስህተት ነው የሚል እምነት ካለዎት፡** የፍትሐብሔር እርምጃዎች ቅርንጫፍን (ሲቪል አክሽን ብራንች) በ202-879-1133 ያነጋግሩ። ይህን እርምጃ ያላደረጉ ከሆነ አካሉ ወይም ጠበቃው በሽምግልና በሙላት መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል።

**5. አካላት በባለ ብዙ-በር ምትክ በግል ሽምግልና (ፕራይቬት ሚድዬሽን) መሳተፍ ይችላሉ፡** ዳኛው የፈቀደ ከሆነ፣ አካላት በባለ ብዙ-በር ሽምግልና ምትክ በግል ሽምግልና መሳተፍ ይችላሉ። በግል ሽምግልና የሚሳተፉ አካላት በዚህ ሰነድ በቁጥር# 1 የተቀመጠውን የመሳተፍ መመሪያ ተገዢ ናቸው።

**6. ከሽምግልና በፊት ስምምነት ላይ ቢደርሱ ጠበቆች ባለ ብዙ-በርን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡** የጉዳዩ መፍቻ ሰነድ (*ፕረሰፒ*) ዋናውና አንድ ቅጂ በክለርክ ቢሮ ፋይል መደረግ ይኖርበታል። አንድ ቅጂ ደግሞ ወደ ባለ ብዙ-በር ክፍል መላክ ይኖርበታል።

**7. ሁሉም አካላት ከተስማሙ የሽምግልና ቀጠሮ እንዴ ማስቀየር ይቻላል፡** በሁለቱም አካላት ስምምነት አንድ የሽምግልና ቀጠሮ ቅየራ ጥያቄ ፍርድ ቤት ሊፈቀድ ይችላል። ይህ የሚሆነው የሲ.ኤስ.ኤስ. እና ኤም.አር.ሲ. መመለሻ ቀናት በፊት (ሽምግልና ከሚደረግበት 14 ቀናት አስቀድሞ) ሲሆንና፣ ወደ ኢሜይል አድራሻ CivilMRC-CSS@dcsc.gov በመላክ ነው። በተጨማሪ፣ የተስማማችሁባቸው ቀናት እና ጊዜያት ያለበት፣ አዲሱ ቀን ጥያቄ ከተደረገበት ቀን ቢያንስ ከ14 ቀናት በኋላ መሆን ይኖርበታል፣ ለተቀናቃኝ ጠበቃ(ቆች) ቅጂ በመላክ መሆን

ይኖርበታል። ሁሉም የፍትሐብሔር ሽምግልናዎች የሚደረጉት በማክሰኞ፣ እሮብ ወይም ሀሙስ ቀናት በ9ኤ.ኤም. ወይም 11ኤ.ኤም. ነው። ሁሉም ሌሎች ተከታይ የተለዋጭ ቀጠሮ ጥያቄዎች በአቤቱታ (ሞሽን) መልክ ለተመደበው ዳኛ መቅረብ ይኖርባቸዋል።

## ሽምግልና በሚደረግበት ቀን፡ መደረግ ያለባቸው ነገሮችና መረጃዎች

**8. ከተመደበው የሽምግልና ሰአት 15 ደቂቃ አከባቢ አስቀድመው መምጣትዎን ያሳውቁ፡** የፍትሐብሔር ሽምግልናዎች የሚደረጉት በ1ኛ ፎቅ ህንጻ ሲ. (C)፣ 410 E Street NW ነው። እንደደረሱ በካውንተሩ (እንግዳ መቀበያ) በሚኖረው ኬዝ ማናጀር ዘንድ መምጣትዎን ያሳውቁ (እየዘገዩ ከሆነ እባክዎ እንግዳ ተቀባያችንን በስልክ ቁጥር 202-879-1549 በመደወል ያሳውቁ)።

**9. ሽምግልና ለ2 ሰአታት አከባቢ ይዘልቃል፡** የጊዜ መስፈርት ባይኖርም፣ ቢያንስ ለ2 ሰአታት ያህል እንዲያቅዱ እንጠይቃለን።

## ስለ ሽምግልና ሂደቱ

**10. የሽምግልና ሂደቶች ሚስጥራዊ ናቸው፡** በመርሀግብሩ መጀመሪያ አካላቱ የመርሀግብሩ ምስጢራዊ መሆኑ እንደገባቸው ለማሳየት "ሽምግልና ለመቀመጥ እስማማለሁ" በሚል ሰነድ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ። በዚህ ጉዳይ በሽምግልና መርሀግብር የተነገሩ ሁሉም ነገሮች፣ በሽምግልና ጊዜ የተዘጋጁ ወይም የተሰጡ ማሳሰቢያዎችና ሰነዶችም ጭምር፣ D.C. Uniform Mediation Act, §16-4207 በሚያዘው መሰረት በምስጢር የሚያዙ ናቸው። ምስጢራዊነቱ ተፈጻሚ የማይሆንበት ሁኔታዎች፡ አላግባብ መጠቀም፣ ቸልተኝነት፣ መተው፣ ብዝበዛ ወይም ማስፈራራቶች እና/ወይም አካላዊ ጉዳት የመፈጸም እቅድ መግለጫዎች ካሉ ሲሆን፣ እነዚህ የመሳሰሉ የያዙ መግለጫዎች በሽምጋዩ ወይም በሰራተኞች በምስጢር ላይያዙ ይችላሉ።

**11.ሽምጋይ መጀመሪያ ከሁሉም አካላት ጋር ይገናኛል፡** በመቀጠል ከያንዳንዱ አካል ለየብቻ እንደየአስፈላጊነቱ ሊገናኝ ይችላል። ይህ የሚሆነው፣ አስፈላጊ ነገሮች ለማብራራት እና አካላቱ ለስምምነቱ ወሳኝ ናቸው ተብለው ለሚታዩ ነገሮች ምስጢሩ የተጠበቀ ነው በሚል እሳቤ ውስጥ በመሆን እንዲናገሩ ለማድረግ ነው። ከአካላቱ ለብቻና በጋራ ለበርካታ ጊዜ በመገናኘት ሽምጋይ ለሁለቱም አካላት ሊያረካ የሚችል ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ለማማቻቸት ይሞክራል።

**12. በሽምግልና እልባት ያገኙ ጉዳዮች፡** ጉዳዩ በሽምግልና እልባት ካገኘ፣ የስምምነቱ ሰነድ *(ፕረሰፒ)* ወይም ሌላ ጉዳዩ በስምምነት እልባት እንዳገኘ የሚያሳይ ሰነድ ቅጂ ለባለ ብዙ-በር ክፍል ኬዝ ማናጀር በስነ ስርአት ፋይል ማድረግ ያስፈልጋል። አካላቱ ፍርድ ቤቱ እንዲያጸድቅላቸው የሚፈልጉ ከሆነ፣ የባለ ብዙ-በር ክፍል ጉዳዩ በሚያየው ዳኛ ጉዳዩ የደረሰበት የሚታይበት ቀጠሮ (ስታተስ ሂሪንግ) ያስይዛል። ስምምነቱ ፍርድ ቤት እንዲያጸድቀው አቤቱታ ፋይል የማድረግ የአካላቱ ሀላፊነት ነው። አቅመ አዳም ያልደረሱ አካላት ያሉበት

ስምምነት በፍርድ ቤት መጽደቅ እንደሚኖርባቸው ልብ እንዲሉ ያስፈልጋል። D.C. Code § 21-120 (2001) *ይመልከቱ።*

**13. በሽምግልና እልባት ያላገኙ ጉዳዮች፡** ጉዳዮ በስምምነት እልባት ካላገኘ በመርሀግብር ትእዛዙ እንደተመለከተው ጉዳዩ ወደ ቅድመ-ክርክር (ፐሪትራያል) ኮንፈረንስ እና ወደ ክርክር ይቀጥላል።

**ሽምግልና በተመለከተ ጥያቄዎች አለዎት ወይም ልዩ ማመቻቸቶች (አኮመዴሽንስ) መጠየቅ ይፈልጋሉ? ባለ ብዙ-በርን በስልክ ቁጥር 202-879-1549 ይደውሉ**

**በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሱፒሪየር ፍርድ ቤት**
**የባለ ብዙ-በር አለመግባባት መፍቻ ክፍል**

የሽምግልና ዝግጁነት የምስክር ወረቀት እና ምስጢራዊ የስምምነት መግለጫ ፋይል አደራረግ መመሪያዎች

ጠበቆች የሽምግልና ዝግጁነት የምስክር ወረቀትን (ኤም.አር.ሲ.) እና ምስጢራዊ የስምምነት መግለጫን (ሲ.ኤስ.ኤስ.) በባለ ብዙ-በር ክፍል፣ ሽምግልና ከሚደረግበት **14 ቀናት** አስቀድመው፣ ፋይል ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ አጠቃላዩ የሽምግልና ትእዛዝ ያስቀምጣል። በጠበቃ ያልተወከሉ አካላት ሲ.ኤስ.ኤስ. ብቻ ፋይል ማድረግ ይኖርባቸዋል። ***ኤም.አር.ሲ. እና ሲ.ኤስ.ኤስ. በጊዜው ፋይል ካልተደረጉ ባለ ብዙ-በር ክፍል ሽምግልናውን በመሰረዝ ጉዳዩ ያለበት ደረጃ የሚታይበት ቀጠሮ (ስታቱስ ሂሪንግ) ጉዳዩ በሚያይ ዳኛ እንደሚያስይዝ ለአካላቱና ለጠበቆቻቸው ያስጠነቅቃል።***

**ማድረስ፡** የተሞሉ የኤም.አር.ሲ. እና ሲ.ኤስ.ኤስ. ቅጾች በኢሜይል CivilMRC-CSS@dcsc.gov እንቀበላለን። ፋይል ማድረግዎን የሚያሳይ ምላሽ ይቀበላሉ። ለመዝገብ አያያዝ ይጠቅም ዘንድ፣ ከ5፡00ፒ.ኤም. በኋላ የተላኩ የኤም.አር.ሲ. እና የሲ.ኤስ.ኤስ. ቅጾች በሚቀጥለው የስራ ቀን እንደደረሱ ነው የሚቆጠሩት። ኤም.አር.ሲ. እና ሲ.ኤስ.ኤስ. በኢሜይል መላክ የማይችሉ ከሆነ እባክዎ በአካል ወይም በፖስታ ወደ ለባለ ብዙ-በር አለመግባባት መፍቻ ክፍል- Multi-Door Dispute Resolution Division, 410 E Street, N.W., Suite 2900, Washington, D.C. 20001 ያድርሱ። ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5፡00 ፒ.ኤም. ባሉ ሰአታት መድረስ ይኖርባቸዋል፣ *ለኤም.አር.ሲ. እና ሲ.ኤስ.ኤስ. ቅጾች ከስራ ሰአት በኋላ ፋይል የሚደረግበት ሳጥን የለም።*

ኤም.አር.ሲ. እና ሲ.ኤስ.ኤስ. ቅጾች ወደ ፍትሐብሔር ክፍል ወይም ሌላ ከስራ ሰአት በኋላ ፋይል ማድረጊያ ሳጥን ያለበት ቦታ አያድርሱ። በባለ ብዙ-በር ክፍል በስነ ስርአት ፋይል ማድረግ ኤም.አር.ሲ. እና ሲ.ኤስ.ኤስ. ቅጾች ምስጢራውነታቸው የተጠበቀ እንደሚሆን ያደርጋል፣

በተጨማሪ በፍርድ ቤቱ የጉዳይ ጃኬት ፋይል አይደረጉም ለጉዳዩ ከተመደበ ሸምጋይ ውጪም ለማንም አይታዩም። ፋይል አደራረግ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ቢፈልጉ እባክዎ ባለ ብዙ-በር ክፍልን በ202-879-1549 ይደውሉ።

**ሲ.ኤስ.ኤስ.፡** በሲ.ኤስ.ኤስ. የሚያቀርቡት መረጃ እባክዎ ሰፊና ግልጽ ይሁን፣ ይህ መረጃ ለሽምግልና አስፈላጊ ነው። ለሸምጋይ ደጋፊ ሊሆን የሚችል መረጃ እንዲያካትቱ ይበረታታሉ።

**ሽምግልና የሚደረግበት ቀጠሮ የተቀየረ ከሆነ፣ ትክክለኛው ቀን ያለበት የመጀመሪያው ወይም የተከለሰው ኤም.አር.ሲ. እና ሲ.ኤስ.ኤስ. ያስረክቡ።**

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሱፒሪየር ፍርድ ቤት
**የባለ ብዙ-በር አለመግባባት መፍቻ ክፍል**

## የሽምግልና ዝግጁነት የምስክር ወረቀት

የጉዳይ ቁጥር (ኬዝ ናምበር)፡ ________________________________ ሽምግልና የሚደረግበት ቀን፡ _________

የጉዳዩ ስም (ኬዝ ኔም)፡ ________________________________________________________________________________ _________

**አጠቃላይ የሽምግልና ትእዛዝ** በሚያዘው መሰረት፣ የሚከተለውን አረጋግጣለሁ፡

- ከኔ የሚፈለገው ግኝት በሙሉ አጠናቅቄአለሁኝ፣ ወይም ዳኛው ግኝቱ ሳይጠናቀቅ አስቀድመን ሽምግልና እንድናደርግ ፈቅዷል፣
- በሽምግልና ጊዜ ለድርድሩ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ በሂደት ያሉ አቤቱታዎች የሉም፣
- ጉዳዩ በተመለከተ ከደምበኛዬ ጋር ተወያይቼአለሁኝ እና ጉዳዩ በስምምነት እልባት ያገኝ ዘንድ በሽምግልና በሚደረጉ ድርድሮች በጥሩ እምነት ለመሳተፍ ዝግጁ ነን፣
- ምስጢራዊ የስምምነት መግለጫዬ ፋይል ተደርጓል፣
- ደምበኛዬ(ኞቼ) በአካል ይሳተፋሉ ወይም በአካል እንዳይሳተፉ ዳኛ ፈቅዷል፣
- ሁሉም አካላትና ማንኛውም የጉዳዩ አካል ያልሆነ ሰው፣ ነገር ግን ጉዳዩን በስምምነት እልባት እንዲያገኝ ፈቃዱ አስፈላጊ የሆነ ሰው፣ ይኖራል፣ ወይም በCivil Rule 16(j) መሰረት ዳኛው እንዳይኖሩ ፈቃድ ሰጥቷል።

<u>እባክዎ ከሚከተሉት **አንዱን** ይምረጡ፡</u>

☐ ከታች የፈረመው ጠበቃ ለሽምግልና **ዝግጁ ነው**፣ ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉም መስፈርቶችም ያሟላል።

☐ ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ባያሟላም፣ የፈረመው ጠበቃ ጉዳዩ በስምምነት እልባት ያገኝ ዘንድ በሽምግልና በሚደረጉ ድርድሮች በጥሩ እምነት ለመሳተፍ **ዝግጁ ነው**።
  - እባክዎ ያብራሩ፡ (ለምሳሌ፡ ያልተቋጨ ግኝት ስምምነት ለመድረስ ለሚደረጉ ድርድሮች እንቅፋት አይሆንም)________________________________________________

☐ ከታች የፈረመው ጠበቃ ከታች ከተዘረዘሩት በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ምክኒያቶች ለሽምግልና **ዝግጁ** አይደሉም (ይህን ከመረጡ፣ ሽምግልናዎ **ተሰርዞ** ጉዳዩ የት ደረጃ እንዳለ ለማየት ዳኛ ፊት ሊቀርቡ **ይችላሉ**። ማንኛቸውም ስረዛዎች ለማረጋገጥ ኬዝ ማናጀር ክትትል

ያደርጋል)፡

- ☐ ግኝት አልተጠናቀቀም
- ☐ በሽምግልና ጊዜ የስምምነት ድርድሮች ለማድረግ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ በሂደት ያሉ አቤቱታ(ዎች) አሉ
- ☐ ደምበኛዬን ማግኘት አልቻልኩም
- ☐ የባለ ጉዳዩ ጠበቃ መሆኔን ለማቆም ያቀረብኩት በሂደት ያለ አቤቱታ አለኝ

ማረጋገጫ ያደረገው፡ የተረከበበት ቀን፡

_______________________________ _______________________

የ ______________________________________ ጠበቃ

***ይህ ቅጽ ሽምግልና ከሚደረግበት ቢያንስ ከ14 ቀናት በፊት ፋይል መደረግ ይኖርበታል። የተሳሳቱ መግለጫዎች ማቅረብ እገዳዎች እንዲጣሉ ሊያስደርግ እንደሚችል ጠበቃዎች ልብ እንዲሉ ይመከራሉ።***

**ምስጢራዊ የስምምነት መግለጫ**

**የባለ ብዙ-በር አለመግባባት መፍቻ ክፍል**

ዳኛ _____________________ የጉዳይ ቁጥር (ኬዝ ናምበር)____________________

የጉዳይ መግለጫ (ኬዝ ካፕሽን) ______________________________________________

ይህ ጉዳይ ቀጠሮ የተያዘው ለ፡

ሽምግልና ኮንፈረንስ በ _______________ በ · 9:00 · 11:00 ነው

**ከሚሳተፉ አካላት አስተርጓሚ የሚያስፈልገው አለ? · አዎ · አይ**

**ምላሽዎ አዎ ከሆነ፣ እባክዎ የፍርድ ቤት አስተርጓሚው በምን ቋንቋ ለማስተርጎም ሞያዊ ፈቃድ (ሰርቲፋይድ መሆን) እንደሚያስፈልገው ይጥቀሱ፡**

______________________________________________________

**ሽምጋይ እንዲኖረው የሚፈለገው ኤክስፐርቲዝ (እውቀት)፡ ______________________**

(እባክዎ ይግለጹ)

አስረካቢው፡

<u>አንዱ ላይ ምልክት ያድርጉ</u>

ጠበቃ ወይም *ጠበቃ የሌለው* አካል

- ከሳሽ
- ተከላካይ
- 3ኛ አካል ከሳሽ
- 3ኛ አካል ተከላካይ

የስልክ ቁጥር

የኢሜይል አድራሻ

**እርስዎ የሚወክሏቸው አካላት <u>ሁሉንም</u> ይዘርዝሩ። (አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ገጽ ያያይዙ)። ሁሉም አካላት የተዘረዘሩ ከሆነ፣ በዚህ ለሚወክሏቸው ሁሉም አካላት አንድ የስምምነት መግለጫ ፋይል ማድረጉ በቂ ነው።**

የአካሉ ስም

የአካሉ ስም

የአካሉ ስም

የአካሉ ስም

**እባክዎ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሾች ይስጡ፡**

1. የጉዳዩ ሀቆችና እየተነሱ ያሉ የይገባኛል ጥያቄዎችን በዝርዝር ይግለጹ፡

2. (ከሳሽ ብቻ) የጉዳቶቹ (ኢንጁሪስ) አይነትና ደረጃ፣ እየተጠየቀ ያለውን የገንዘብ እና/ወይም ፍትሀዊ እፎይታ ይግለጹ (እባክዎ እንደነ የጠፋ ደሞዝ፣ የህክምና ወጪዎች፣ ወዘተ፣ ለየብቻ ይዘርዝሩ)፡

3. (ተከላካይ ብቻ) እያደረጓቸው ያሉ ማናቸውም የአጸፋ-የይገባኛል ጥያቄዎች (ካውንተርክለይምስ) ይግለጹ፡

4. በስምምነት ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ የዚህ ጉዳይ ዋጋ እንዴት ይገመግሙታል?

አነስተኛ $___________ ከፍተኛ $___________

5. ጉዳዩ በስምምነት እልባት እንዲያገኝ ያደረጓቸው ማናቸውም አቅርቦቶች/ፍላጎቶች (ኦፈርስ/ዲማንድስ) እና ውይይቶቹ ያሉበት ደረጃ ይግለጹ፡

6(a). (ተከላካይ ብቻ) እያጣሉዋቸው ያሉ የይገባኛል ጉዳዮች በኢንሹራንስ ሽፋን ያላቸው ከሆነ እባክዎ የፖሊሲው ገደብ ያቅርቡ፡

6(b). (ተከላካይ ብቻ) ምላሽዎ አዎ ከሆነ፣ እባክዎ የኢንሹራን ኩባንያው ስምና፣ ጉዳዩ በስምምነት እልባት ለማግኘት ፈቃዱ ሊያስፈልግ ስለሚችል በሽምግልና መርሐግብሩ ይሳተፋል ብለው ተስፋ የሚያደርጉት የይገባኛል ጥያቄዎች ተወካይ (ክለይምስ ረፕረዘንታቲቭ) ስም ይስጡ። (Super. Ct. Civ. R 16(j) ይመልከቱ)።

7. (ከሳሽ ብቻ) ገና ያልተከፈላቸው አበዳሪዎች (አውስታንዲንግ ሊንስ)፣ መጠናቸው፣ እና ከአበዳሪዎች ጋር የተደረጉ ማንኛቸውም ድርድሮች ይዘርዝሩ፡

8. በጉዳዩ እንደ አካል ያልተዘረዘረ፣ ነገር ግን ትርጉም ያላቸው ድርድሮች ለማድረግ በአካል መገኘት ይኖርባቸዋል የሚሉት ማንኛውም ሰው ይዘርዝሩ፡

9. በሽምግልናው ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ (አዎንታዊም አሉታዊም) በአካላቱ መካከል ያሉ ተጓዳኝ ምክንያቶች ወይም ታሪክ ይግለጹ፡

10. ፋይል በተደረጉት ላይ ያልሰፈሩ፣ ነገር ግን አካላቱን ውጤታማ የሆኑ ድርድሮች እንዲያደርጉ ለማድረግ ለሽምጋይ ሊያግዙ የሚችሉ፣ ሽምጋይ ምን ተጨማሪ መረጃዎች ማወቅ ያለበት ይመስሎታል? (የግኝት ቀነ ገደብ ሽምግልና ከሚደረግበት ቀን በፊት እንደሆነ ያስታውሱ።)

____________________________

የገባበት ቀን (ዴት ሳብሚትድ)

**ያስገቡ (ሳብሚት)**